**አገስት 2018 QuickNotes ቅጽ 1**

**የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) 25 አዳዲስ ርእሰመምህራንን እንኳን ደህና መጣችሁ በማለት ይቀበላል።**

ማክሰኞ፣ ሴፕቴምበር 4 የ 2018 - 2019 የትምህርት ዓመት ሲጀመር ከ 163,000 በላይ ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤቶቻቸው ያመራሉ። ከ 850 በላይ መምህራን ተቀጥረዋል፣ እና አዳዲስ ተማሪዎቻቸውን እና ቤተሰቦቻቸውን ለማየት/ለመቀበል በጉጉት የሚጠባበቁ 25 አዳዲስ (ወይም ለት/ቤቱ አዲስ የሆኑ) ርእሰመምህራን አሉ። እነዚህ ርእሰ መምህራን የት/ቤቶቻቸው ማህበረሰቦች እንዲያውቁ የሚፈልጉትን አስደሳች ወይም አዝናኝ የሆነ እውነታ በሞንትጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች የፈጣን መልእክት አምድ ላይ (MCPS QuickNotes) እንዲያካፍሉ ተጠይቀዋል።

**የአንደኛ ደረጃ ት/ቤት**

**ማይክል ዲ. ቤይዊትዝ፣ ክሎቨርሊ/Michael D. Bayewitz, Cloverly**
እኔ የ U2 ባንድ ትልቅ ደጋፊ ነኝ። ኮንሰርት ሲያቀርቡ 21 ጊዜ ተመልክቻለሁ።

**መረድዝ ኤ. ካስፐር፣ ዶ/ር  ቻርለስ አር. ድሪው/Meredith A. Casper, Dr. Charles R. Drew**
በ29 ዓመታት ውስጥ ለአራት የተለያዩ የትምህርት ሥርዓቶች ሠርቻለሁ። ምርጥ የት/ቤት መክፈቻ ቅምሻ ከልጆችዎ ጋር ፎተግራፍ ላይ አብሮ መሆን ነው። ልጆች ብዙ ጊዜ ስለ ት/ቤት ስራዎቻቸዉ በሚያወሩላቸው ጊዜ ወደ ኋላ ተመልሰው ስለእርስዎ ማሰብ ይወዳሉ።

**ማይክል ደብሊው. በርድ፣ ኢስት ሲልቨርስፐሪንግ/Michael W. Burd, East Silver Spring**
እኔ ያደግሁት በ ዊሊያምስፖርት፣ ፔንስልቫንያ/Williamsport, Pennsylvania "the Little League World Series" ቤት ተብሎ የሚታወቅ አካባቢ ነው።

**ካስንድራ ሄፍትዝ፣ ግለን ሄቨን/Cassandra Heifetz, Glen Haven**
እኔ አራተኛ-ትውልድ የትምህርት ባለሙያ ነኝ! የኔ አክስት በኮሎራዶ/Colorado ንባብ ታስተምራለች፣ የእኔ ሴት አያቴ በፔንስላቫንያ መምህርት እና ላይብራሪያን ነበረች፣ የእኔ ቅድመ አያትም በገጠር ፔንስልቫንያ አንድ ክፍል ት/ቤት ውስጥ አስተምራለች። ከአዲሱ ትውልድ ጋር የመማር ፍቅርን ለማስፋፋት በመቀጠሌ ኩራት ይሰማኛል!

**አን ሄፍሊን፣ ግለንላን/Ann Hefflin, Glenallan**
በአስተማሪነት 28ኛ ዓመቴን እና በርእሰመምህርነት አንደኛ ዓመቴን እየጀመርኩ ነው! በማስተማር እና በመማር ሥራ እበረታታለሁ፣ እንደዚሁም ከቤተሰብ፣ ጓደኞች/ወዳጆች ጋር የሚኖረኝን ጊዜ እና ለራሴም/ለብቻዬም የጥሞና ጊዜ ዋጋ እሰጣለሁ።

**ኬሪ፣ ኤል. ዚመርማን፣ ግሪንውድ/Carrie L. Zimmerman, Greenwood**
አራት የአንደኛ ደረጃ ት/ቤት እድሜ ልጆች እናት በመሆኔ ባተሌ ነኝ (ሙዓለህፃናት፣ ሁለተኛ ክፍል፣ አራተኛ ክፍል እና አምስተኛ ክፍል)። ባለቤቴ፣ ልጆች እና እኔ ፓርኮችን እናደንቃለን እና የ Hershey Park የወቅቱ ፓስሆልደሮች ነን።

**ማሪያ ዲ. ዋትሰን፣ ሌይቶንስቪል/Maria D. Watson, Laytonsville**

ከባለቤቴ ጋር እና ከውሻችን ጋር ከቤት ውጪ ጊዜ ማሳለፍ እወዳለሁ። ከት/ቤት ከንውን በኋላ የረፈደም እንኳ ቢሆን ሦስታችንም በየቀኑ —በእግር ለመራመድ እንሞክራለን።

**ክርስቲን ዲ. አበርዶርፍ፣ ፓይኒብራንች/Christine D. Oberdorf, Piney Branch**
ባለቤቴ፣ ወንዱ ልጄ፣ ሴቷ ልጄ እና እኔ ከቤት ውጪ በአካባቢ ፓርኮች እና የእግር መንገዶች ላይ እየቃኘን ጊዜ ማሰለፍ ያደስተናል። እኛ ሁላችንም ግሩም የሆነ የትምህርት ዓመት እስኪጀመር በጉጉት እየጠበቅን ነው!

**ራሄል ሲ. ዱቦይስ፣ ቤያርድ ረስቲን/Rachel C. Dubois, Bayard Rustin**

**ሜጋን ኤች. መርፊይ፣ ሰቨን ሎክስ/Megan H. Murphy, Seven Locks**
የቀድሞ የ MCPS ተማሪ እንደመሆኔ መጠን፣ ለእኔ ይህን ሁሉ ላጎናጸፈኝ የትምህርት ሥርዓት ወሮታውን ለመመለስ ጓጉቻለሁ። ት/ቤት በማልሆንበት ጊዜ፣ ከባለቤቴ እና ከወንድ ልጄ ጋር ጊዜ ማሳለፍ እወዳለሁ!

**ማቲው ኤ.ደቨን፣ ትዊንብሩክ/Matthew A. Devan, Twinbrook**
ያደግሁት በሮቸስተር፣ ኒውዮርክ/Rochester, New York ሲሆን፣ በክረምት ጊዜ ኩሬ ላይ የኔን ስኖውሞባይል መንዳት እና ሆኪ መጫወት ደስ ይለኛል። በትዊንብሩክ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት-Twinbrook Elementary ርእሰመምህር በመሆኔ ደስታ ይሰማኛል። ተማሪዎቻችን በ ጁልየስ ዌስት መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት-Julius West Middle School እና በሪቻርድ ሞንትጎመሪ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት-Richard Montgomery High School የሚጠብቃቸውን ትልልቅ ፕሮግራሞች ተጠቃሚነታቸውን ለማረጋገጥ በጉጉት እንጠብቃለን።

**ዶ/ር አሚይ ጄ. አሎንሶ፣ ዋሽንግተን ግሮቭ/Dr. Amy J. Alonso, Washington Grove**
ከጓደኞች ጋር መጓዝ እወዳለሁ። እኔ ለመጓዝ የምፈልገው ወደ ሜክሲኮ/Mexico ነው። በዚህ ዓመት የተመኘሁትን በጀልባ ተንሳፋፊ ጃንጥላ ከጀልባ ወደ ላይ ሽቅብ ተወንጭፌአለሁ/parasailing!

**ኡድራ ኤም. ዊልሰን፣ ዌስቶቨር/Audra M. Wilson, Westover**
ከቤተሰቤ እና ከጓደኞች ጋር አዳዲስ ምግብ ቤቶችን መሞከር እወዳለሁ እና በአሁኑ ወቅት በ Zagat guide/የጥሩ ሆቴሎች ጠቋሚ መመሪያ አማካይነት በራሴ መንገድ እየበላሁ ነዉ!

**ሎሬታ ኤ. ውድስ፣ ዊህትስቶን/Loretta A. Woods, Whetstone**
የተወለድኩት ጋና፣ ምእራብ አፍሪካ/Ghana, West Africa ነው። እኔ የሁለት በጣም ጎበዝ ወንዶች ልጆች እናት እና በጣም ጠንካራ ሞራል ያለው ፖሊስ ባለቤት ነኝ።

**መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት**

**ሚሼል ሊ. ፎርቱን፣ ቤንጃሚን ባንከር/Michelle L. Fortune, Benjamin Banneker**
እናቴ አስተማሪ ስለነበረች እኔንም ወደ መምህርነት እንድገባ አነሳስቶኛል። በተማሪዎቼ እና በራሴ ልጆች ላይ ከፍተኛ ደረጃ የትምህርት ፍላጎት/ጉጉት እንዲያድርባቸው የማስረፅ ጉጉት አለኝ። በትርፍ ጊዜዬ መሮጥ እና ከቤተሰቤ ጋር ቢች ላይ ጊዜ ማሳለፍ እወዳለሁ።

**ስተፈኒ ኤስ. ሸሮን፣ ብሪግስ ቼኒ/Stephanie S. Sheron, Briggs Chaney**
እኔ የ MCPS ቤተሰብ አካል ነኝ! ባለቤቴ እና እኔ ሁለታችንም የ MCPS ሠራተኞች ነን እና የእኔ የ6 ዓመት ወንድ ልጄም እንደዚሁ በካውንቲው አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ይማራል። ለትምህርት ካለን መውደድ በተጨማሪ፣ እንደቤተሰብ ለማድረግ የምንወደው ወደ ባህር ዳርቻ መሄድን ነው።

**ዶ/ር አንመሪ ኬ. ስሚዝ፣ ኖርዝ ቤተስዳ/Dr. Annemarie K. Smith, North Bethesda**
እኔ በአራት ክፍለአህጉራት ኖሬአለሁ፣ ነገር ግን የኋላ ኋላ፣ ከሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የተመረቅሁት ለመጀመሪያ ጊዜ ት/ቤትን በርእሰመምህርነት እንድመራ እድል በተሰጠኝ ማህበረሰብ ውስጥ ነው!

**ጆን ግሪን፣ ጆን ፑል Jon Green, John Poole**

**ሻውና-ኬይ ጄ. ጆራንድባይ፣ ስላይጎ/Shauna-Kay J. Jorandby, Sligo**
ፍጹም ወደ አዲስ መጽሐፍ ውስጥ መነከርን እወዳለሁ እና ተማሪዎችም በየጊዜው ለኔ አዳዲስ መጽሐፍትን ይጠቁሙኛል። ብዙ የመጻሕፍት ክለቦች ደጋፊ አባል እንደሆንኩ ይሰማኛል።

**ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት**

ብራንዲስ ሲ. ኸከርት፣ ዊንስተን ቸርችል/Brandice C. Heckert, Winston Churchill

ካሪይ ዲ. ዲሚክ፣ ጌትስበርግ/Cary D. Dimmick, Gaithersburg

**ኤሊዛቤት ኤል. ቶማስ፣ ኲዊንስ ኦርቻርድ/Elizabeth L. Thomas, Quince Orchard**
በሩጫ ክዉነቶች ላይ ዉድድር፣ እንደ Ragnar, Warrior Dash, Savage, እና Rock N Roll እና የግማሽ ማራቶን ውድድሮች በመሳሰሉት ላይ መሳተፍ እወዳለሁ።

**ዶ/ር ኤሪክ ኤል. ሚነስ፣ ሸርውድ/Dr. Eric L. Minus, Sherwood**
ትምህርትዎን በከፍተኛ አቅም/ጉልበት እና ለሚጠበቀዉ አፈፃጸም ጠንክሬ እሰራለሁ በሚል መንፈስ መያያዝ ጥሩ ነው። እርስዎ ለራስዎ ከሚወሰኑት ገደብ/ከሚያስቀመጡት ልክ በላይ ማንም ሰው ለእርስዎ ከፍተኛ የሚጠበቅ ልክ ለመፍጠር አይችልም። ያለው አማራጭ "ልቀት" ብቻ ነው።

**ሮበርት ደብሊው. ዶድ፣ ዋልት ዊትማን/Robert W. Dodd, Walt Whitman**
እኔ በ MCPS በሦስቱም ደረጃዎች (በአንደኛ ደረጃ፣ በመካከለኛ ደረጃ፣ እና በሁለተኛ ደረጃ) በርእሰ መምህርነት ካገለገሉት ሦስት የትምህርት ባለሙያዎች በይፋም ባይሆን አንዱ ነኝ።

**ልዩ ት/ቤት**
**ስቴፈኒ ሻኡልበርገር፣ ሮክ ተሬስ ት/ቤት (ተጠባባቂ)/Stephanie Schaufelberger, Rock Terrace School (acting)**

**የ 2018-2019 የትምህርት ዓመት ዝግጅት የመቆጣጠርያ ዝርዝር፡-**

ወላጆች፣ አዲስ የትምህርት አመት መጀመርያ ነው! ስኬታማ ዓመት እንዲሆንላችሁ በሚያስፈልጋችሁ መረጃ መታጠቃችሁን ለማረጋገጥ እንዲያግዛችሁ የተዘጋጀ የመቆጣጠርያ ዝርዝር ይሄውና፡-

- ✓ ይመዝገቡ ለ myMCPS parent portal! myMCPS ማለት የመካከለኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችን የትምህርት ውጤት እና የቤት ስራዎችን ወላጆቻቸው ለመከታተል እንዲያስችላቸው የተዘረጋ አውታረ-መረብ ነው። የአንደኛ ደረጃ እና ሁለተኛ ደረጃ ወላጆች አዲሱን myMCPS app/መተግበሪያ በመጫን መገናኘት ሲቀጥሉ ይችላሉ። app/መተግበሪያ በነፃ በ iTunes እና Google Play ላይ ይገኛል።

- ✓ የልጅዎን የድንገተኛ ጊዜ መረጃ/ኢንፎርሜሽን ቅጽ ይሙሉ

- ✓ በ myMCPS portal ላይ የአካባቢ ት/ቤት ድንገት መዘጋት ካለበት፣ ቢታመም/ብትታመም እና ሌሎችም አስፈላጊ/አፋጣኝ ነገሮች ሲያጋጥሙ እርስዎን ለማግኘት እንዲቻል የሚጠቀሙበት መገናኛ ነው። በትምህርት ዓመቱ ውስጥ ስለ እርስዎ የመረጃ/ኢንፎርሜሽን ለውጥ ከተደረገ ት/ቤቱ እንዲያውቀው መደረጉን እርግጠኛ ይሁኑ።

- ✓ በልጅዎ ት/ቤት በበጎ ፈቃደኝነት ለማገልገል የሚፈልጉ ከሆነ፣ ስለ ልጅ ጉስቁልና እና ችላ መባል የስልጠና ክፍል/Child Abuse and Neglect training modules የበጎፈቃድ አገልጋዮችን ስልጠና ያጠናቁ።

- ✓ የ 2018-2019 ቀን መቁጠርያ ይመልከቱ፣ ያትሙት ወይም ከድረ-ገፅ ማስተላለፊያ-ላይ የዋና ዋና ቀኖች/ድርጊቶች መረጃ/ኢንፎርሜሽን እንዲኖርዎት ያስፈልጋል። ለእርስዎ በጣም አስፈላጊው የትኛው እንደሆነ እንዲመለከቱት ካላንዳሩ የራስዎንም ካላንደር እንዲያዳብሩ አሳታፊ ነው።

- ✓ የልጅዎ ያውቶቡስ መስመር መረጃ ይኑርዎት። ስለ አውቶቡስ መስመሮች ጥያቄ ያላቸው ወላጆች መልሶችን ከዚህ ለማግኘት ይችላሉ።

- ✓ በልጅዎ አካውንት የምግብ ገንዘብ ለመጨመር በ MySchoolBucks መጠቀም ያስታውሱ። ይሄ አሠራር ልጅዎ በየቀኑ ወደ ት/ቤት ገንዘብ ይዞ/ይዛ መምጣትን ያስወግዳል። የት/ቤት ምግብ ቤቶች በጥሬ ገንዘብ ወይም በቼክ ቅድሚያ ክፍያም ይቀበላሉ።

- ✓ ከ 7ኛ እስከ 11ኛ ክፍል የሚማሩ ልጆች ካሉዎት የትምህርት ዓመት ከመጀመሩ በፊት የ Tdap እና MCV4 ክትባት መውሰዳቸውን ያረጋግጡ። የሜሪላንድ የክትባት ግዴታዎችን የማያሟሉ ተማሪዎች የክትባት ማስረጃ እስኪያቀርቡ ድረስ ት/ቤት ከመከታተል ይታገዳሉ።

- ✓ ስለ ት/ቤት ህጎች እና ደንቦች የበለጠ ይወቁ።

- ✓ በ ት/ቤት መክፈቻ-ምሽት "Back-to-School Night" በልጅዎ ት/ቤት ለመገኘት ፕላን ያድርጉ።

- ✓ የእኛን digital citizenship webpage በማህበራዊ የመገናኛ መገልገያዎች እና ሌሎች ዲጅታል የማህበራዊ ሚዲያ እንዴት ኃላፊነት በተሞላበት መንገድ መጠቀም እንደሚቻል ልጅዎን ለመርዳት እንደሚችሉ ለማወቅ ድረ ገጻችንን ይጎብኙ።

- ✓ ስለ Parent Academy ለማወቅ በነፃ የሚሰጥ አውደጥናት/ላይ መሳተፍ እንዳለብዎት ይገንዘቡ።

- ✓ የትምህርት አመቱን በሞላ ከ MCPS ጋር ግንኙነትዎን ሳያቋርጡ ይቀጥሉ። በትዊተር/Twitter ይከታተሉን (@mcps) እና በፌስቡክ/Facebook (/mcpsmd)፣ YouTube መስመራችን ላይ ይመዝገቡ (/MCPSTV)፣ ይመዝገቡ AlertMCPS፣ MCPS TV ይመልከቱ፣ ይመዝገቡ ለmyMCPS parent portal።

**የት/ቤት መክፈቻ የመጀመሪያ ቀን ፎቶዎችዎን ይላኩልን**

ልጅዎ ሙአለህፃናት የሚ(ምት)ጀምርበት ቀን ይሁን ወይም የመጨረሻ አመት ተማሪም ቢ(ብት)ሆን ት/ቤት የሚከፈትበት የመጀመርያው የትምህርት ቀን ለወላጆች ምንጊዜም ልዩ ጊዜ ነው። የሚመርጡትን የመጀመርያው-የት/ቤት-ቀን ፎቶግራፎች በመስጠት በዲስትሪክቱ ዙርያ አስደሳችና የማይረሱትን ወቅቶች እንድንጨብጥ ይተባበሩን። ከማክሰኞ ጠዋት ጀምሮ በርካታ ፎቶግራፎች በዲስትሪክት አውታረ-መረብ እና በማህበራዊ የመገናኛ ድረ-ገጾች ላይ ይቀርባሉ።

በኢ-ሜይል፦ ወላጆች የሚሻለውን የትምህርት -መጀመርያ-ቀን አግዳሚ ፎቶ መርጠው በ.jpeg file (4 MB ያልበለጠ) ወደ pio@mcpsmd.org መላክ አለባቸው። እባክዎ የልጅዎን ስም፣ የክፍል ደረጃ እና ት/ቤት አብረው ይላኩ (የመጨረሻ ስም አይታተምም)።

ለማህበራዊ ሚድያ፣ ወላጆችና ተማሪዎች በሀሽታግ #MCPS1stday በመጠቀም ትዊተር ላይ ፎቶግራፎች መለጠፍ ይችላሉ። ከተለጠፉት ጥቂቶቹን በMCPS Twitter feed እንደገና ትዊት ይደረጋሉ።

ፎቶውን ሲልኩልን፣ በ MCPS አውታረ-መረብ እንዲታተም ወላጆች ተስማምተዋል ማለት ነው። ጥያቄ ካለዎት Department of Public Information and Web Services በስልክ ቁጥር ፡-240-740-2837 ተገናኙ። ወይም በ pio@mcpsmd.org ኢ-ሜይል ያድርጉልን።

**ሴፕቴምበር ላይ ክሊኒኮች በነፃ ክትባት ይሰጣሉ።**

የሜሪላንድ ስቴት ከ7ኛ እስከ 11ኛ ክፍል የሚማሩ ተማሪዎች በጠቅላላ የትምህርት ዓመቱ ከመጀመሩ በፊት የ Tdap (Tetanus-diphtheria-attenuated pertussis) እና አንድ meningococcal (MCV4) ክትባቶችን መውሰድ እንዳለባቸው ያስገድዳል።

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎት ዲፓርትመንት/መምሪያ ሠራተኞች በካውንቲው ውስጥ በተለያዩ አካባቢዎች ለሚገኙ ተማሪዎች በመስከረም ወር የ Tdap እና MCV4 ክትባቶችን በነፃ ይሰጣሉ። ለመጀመሪያ ጊዜ በሜሪላንድ ት/ቤት ስምንተኛ፣ 9ኛ፣ 10ኛ፣ እና 11ኛ ክፍል የሚመዘገቡ ተማሪዎች ተፈላጊ መስፈርቶችን ለማሟላት ክትባቶችን መውሰድ አለባቸው። ቀጠሮ ኣያስፈልግም ነገር ግን ወላጅ ወይም ሌላ ኣዋቂ ሰው መገኘት ይኖርበታል። እባክዎ ወደ ክሊኒክ ሲመጡ የልጁን/የልጅቱን የክባት ማስረጃ ይዘው ይምጡ።

የክሊኒኮችን የጊዜ ሠሌዳ ይመልከቱ፡-

ስለ ክሊኒኮች የበለጠ መረጃ ለማግኘት በስልክ ቁጥር፡- 240-777-1050 ይጠይቁ።